

# የመንጃ ፈቃድዎን ለማግኘት የሚወሰዷቸው እርምጃዎች

ወቅታዊ የመንጃ ፈቃድ ሳይኖር በምዕራብ አውስትራሊያ ማሽከርከር ሕገ-ወጥ ተግባር ነው። እነዚህን ሕጎች ተላልፎ መገኘት፡- በምዕራብ አውስትራሊያ ፖሊስ ያስከስሳል፣ ፍርድ ቤት ያስቀርባል፣ ቅጣት ያስጥላል፣ እስር ያስፈርዳል እንዲሁም ጉዳት በደረሰበት ሰው ክስ ሊያስመሠረትብዎ ይችላል።

---

## የምዕራብ አውስትራሊያ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት 6 ደረጃዎችን ማለፍ ይኖርብዎታል።

### 1ኛ ደረጃ የለማጅ ፈቃድ

- የመንገድ ሥነ-ሥርዓት ደንቦችን በተመለከተ የቃል ወይም የኮምፒውተር ፈተና መውሰድ ይጠበቅብዎታል።
- እንደ መታወቂያ ያገለግል ዘንድ የልደት የምሥክር ወረቀትዎን፣ ፓስፖርትዎን፣ ቪዛዎን ወይም የዜግነት የምሥክር ወረቀትዎን ማቅረብ ይኖርብዎታል።
- እንዲሁም ፊርማዎንና አሁን ያሉበትን አድራሻ ለማረጋገጥ የሕክምና እንክብካቤ ካርድ፣ የሜዲኬር ካርድ ወይም የባንክ ካርድና ሰነዶችን መውሰድ ይኖርብዎታል።
- የተወሰነ ገንዘብ መክፈል ይጠበቅብዎታል። ገንዘቡን የሚከፍሉት ለቃል ፈተናውና ፈተናውን ካለፉ ደግሞ ለለማጅ ፈቃዱ ይሆናል። እንዲሁም ከፍያው ለአንድ የተግባር ፈተና የሚያስፈልገውን ክፍያ የሚጨምር ይሆናል።

### 2ኛ ደረጃ ማሽከርከርን መማር

- ከተመሳሳይ ክፍል መንጃ ፈቃድ ካወጣ አራት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነው ሰው ጋር ሆነው ማሽከርከርን መማር መጀመር ይችላሉ።
- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ የለማጅ ፈቃዱን መያዝ ይኖርብዎታል።
- ማሽከርከር በሚለማመዱበት ጊዜ ሁሉ ተሽከርካሪዎ ላይ L የሚል ምልክት ማድረግ ይኖርብዎታል።
- አልኮል ወስዶ ማሽከርከር አይፈቀድም።

### 3ኛ ደረጃ የአሽከርካሪነት የተግባር ፈተና

- እድሜዎ ቢያንስ 16 ዓመት ከ6 ወር ሊሆን ይገባል።
- በሚፈተኑበት ጊዜ ጥሩ ተሽከርካሪ ሊጠቀሙ ይገባል። የለማጅ ፈቃዱን በሚያገኙበት ጊዜ ለመጀመሪያው የተግባር ፈተናዎ የሚያስፈልገውም ክፍያ አብሮ ይሸፈናል። በመጀመሪያው ወቅት ካላለፉ ከዚያ በኋላ ለሚወስዱት ለእያንዳንዱ ፈተና መክፈል ይጠበቅብዎታል።

### 4ኛ ደረጃ መመዝገቢያ ደብተር

- የአሽከርካሪነት ፈተናውን ሲያልፉ የመመዝገቢያ ደብተር ይሰጥዎታል።
- የመመዝገቢያ ደብተሩን ለማግኘት የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይጠበቅብዎታል።
- በሌላ ሰው ክትትል ቢያንስ ለ25 ሰዓታት ማሽከርከር ይኖርብዎታል።
- እያንዳንዱን የልምምድ ጊዜ በዚህ ደብተር ላይ መመዝገብ ይኖርብዎታል።
- ሕጋዊ ሰነድ ስለሆነ እዚያ ላይ የሚመዘገበው ማንኛውም ነገር እውነተኛ፣ የተፈረመበትና በምሥክር የተረጋገጠ መሆን ይኖርበታል።
- በሚያሽከረክሩበት ጊዜ ሁሉ ተሽከርካሪዎ ላይ L የሚል ምልክት ማድረግ ይኖርብዎታል።
- አልኮል ወስዶ ማሽከርከር አይፈቀድም።

### 5ኛ ደረጃ የአደጋዎች ፈተና

- መንጃ ፈቃድዎን ከማግኘትዎ በፊት አንድ አሽከርካሪ የሚያጋጥሙትን የተለያዩ ሁኔታዎች መወጣትና ከማሽከርከር ጋር የተያያዙ አስተማማኝ ውሳኔዎችን ማድረግ ይችሉ እንደሆነ ለማረጋገጥ በኮምፒውተር የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ ይኖርብዎታል።
- ዕድሜዎ 17 ዓመት ሊሆን ይገባል።
- የመመዝገቢያ ደብተርዎ በሌላ ሰው ክትትል የሚያከናውኑትን የ25 ሰዓታት ልምምድ ያጠናቀቁ መሆኑን የሚያሳይ እንዲሁም በእርስዎና በአስተማሪዎ ወይም በተቆጣጣሪዎ የተፈረመ መሆን ይኖርበታል።
- የመመዝገቢያ ደብተሩንና መታወቂያዎን ይዘው ወደ ፈቃድ ሰጪ ማዕከሉ ወይም ወደ ፈቃድ ወኪሉ ይሂዱ።
- ለፈተናው ለመቀመጥ የተወሰነ ገንዘብ መክፈል ይጠበቅብዎታል።

### 6ኛ ደረጃ ፈቃድ

- ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት ሁሉ አጠናቅቀው ፈተናዎችን በሙሉ ሲያልፉ ፈቃድዎን ያገኛሉ።
- ለፈቃዱ ፎቶ እንዲነሱ ይደረጋል።
- ፈቃድዎን ለማግኘት የተወሰነ ገንዘብ እንዲከፍሉ ይጠበቅብዎታል።
- አልኮል ወስዶ ማሽከርከር አይፈቀድም።

Amharic 16/05/2008

Department for Planning and Infrastructure
Government of Western Australia

DRIVE SAFE. ARRIVE SAFE.
SPEED AND RED LIGHT CAMERA FUNDED PROJECT
www.officeofroadsafety.wa.gov.au

በዌስተርን አውስትራሊያ ጎዳናዎች ላይ የሚጠፋውን ሕይወት ለመታደግ የተዘጋጀውን የዚህን መመሪያ ወጪ የሸፈነው የምዕራብ አውስትራሊያ የኢንሹራንስ ኮሚሽን ነው።